# የአንዷት ፍልስጤማዊት ሴት ተጋድሎን የሚያሳይ የቪድዮ ፊልም

ሰላም  እንደምን ሰንብታችኋል?

ዛሬ ይገፍላችሁ የመጣሁት ልብን የሚነካ የአንዷት ፍልስጤማዊት ሴት ተጋድሎን የሚያሳይ የቪድዮ ፊልም ነው. ያገኘሁትም www.youtube.com በሚለው ዌብ ሳይት ላይ ሲሆን የዚህችን ወጣት ሴት ሁኔታ ስመለከተው የዛሬ 35 ዓመት አካባቢ ለወንድሞቻቸው እና ለወገኖቻቸው ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን ያሳለፉትን ወጣት ሴቶችና ወጣት ወንድ የኢሕአፓን አባላቶችን እንዳስታውስ አደረገኝ.

ምንም እንኳን በዚያን ወቅት በጣም ትንሽ ልጅ ብሆንም ብዙዎቻችሁ እንደምታስታውሱት ቁርጠኛ የኢትዮጵያ ልጆችና ውድ የኢሕአፓ ጓዶች ወንድሞቻቸውን ለፋሺስቱ ደርግ አሳልፈው ላለመስጠት ሲሉ የራሳቸውን ሕይወት ከወንድሞቻቸው ሕይወት አስቀድመው በመስጠት፤ የሚመጣባቸውን ዛቻ፣ ዱላ እና መከራ ሳይፈሩ፤ በእበላ ባይ ካድሬዎች፤ ሰውን የራሱን ሥጋ መትሮ ማብላት፤ ጥፍሮቹን መንቀል፤ በፈላ ዘይት ውስጥ መዝፈቅ፤ በኤሌክትሪክ በመጥበስ፤ አፍንጫን በፒንሳ ቦጭቆ መጣል፤ በሴት ብልት ውስጥ ጠርሙስ መጠርመስና ጡቶቿን መቁራጥ፤ በአፋቸው ሽንትና ሠገራ የጠጣ ጨርቅ እየተጎሰጎሰና እጅ እግራቸው በገመድ ታሥሮ እጃቸቸውን በጉልበታቸው ላይ እንዲያሳልፉ ተደርጎ ከጉልበታቸው ሥር እንጨት አስገብተው ከፍ ካሉ ሁለት ወንበሮች ወይም ጠረጴዛዎች ላይ ሲያንጠለጥሉዋቸው እግራቸው ወደ ላይ ራሳቸው ወደታች ሲሆን ወፌላላ እያሉ የሚጠሩትን ዘግናኝ የማሰቃያ ዘዴ በመጠቀም የውስጥ እግራቸውን በተለያዩ መሣሪያዎች በመግረፍና በማሰቃየት የጓዶቻቸውን ሥም አሳልፈው እንዲሰጡ (እንዲጠቁሙ) ቢያስገድዷቸውም፤

አያወላውልም ፍጹም ነው እምነቴ
የፋሽስቶች ጥይት ቢደቀን እፊቴ

እያሉ ደረታቸውን ለፋሽስቶች ጥይት እግራችቸውንና መላው ሰውነታቸውን ለፋሽስቶችና ካድሬዎቻቸው ሰጥተው ከወንድሞቻቸው ቀድመው ሕይወታቸውን በመስጠታቸው እስከዛሬ ድረስ የብዙ ንጹሕ ወጣት ደምን እንዳዳኑና ምን ያህል የሚያኮራን ታሪክ ሠርተው እንዳለፉ አሁን በሕይወት የሚገኙት የቀድሞ የኢሕአፓ አባላቶች በኩራት ሲመሰክሩላቸው ስንሰማ ለማመን ያዳግተናል.  ነገር ግን ዛሬም ቢሆን በአገራችንና በሌሎች አገራትም እንደነዚያ ዓይነት ጀግኖች ወጣቶች አልጠፉም. ለዚህም ምስክር የሚሆነን ይህቺ የፍልስጤም ወጣት ሴት ልጅ ናት. ይህች ወጣት የወንድሞቿን ሞት ላለማየት ደረቷን ለታጠቀ የእሥራኤል ወታደር የሰጠችና ወንድሞቿን ከሞት ለመታደግ ያደረገችው ጥረት ለእኔ የዓመቱ የጀግኖች ጀግና ብዬ ለመጥራት ያስችለኛል. ይህችም ወጣት የዛሬ 35 ዓመት አካባቢ እንዲሁ ከወንድሞቻቸው ጐን ቆመው መታገላቸው፤

ሴትና ወንድ አይልም ትግል የጋራ ነው
ደብሬንና ማርታን ምሳሌ ማድረግ ነው

እየተባለ የተዘፈነላቸው ወጣት ሴት የኢሕአፓ ታጋዮችን እንዳስታውሳቸው አድርጎኛል. እንግዲህ በወቅቱ የነበራችሁ ታጋይ ወንድሞቻችን ከኔ በተሻለ ሁኔታ ይህንን ዓይነት ተጋድሎ ሲያደርጉ ሕይወታቸው በደርግ ጥይት የአለፈውን በሺ የሚቆጠሩ የኢሕአፓ ሴት ታጋዮችን ታሪክ እንድታስታውሱት ያስገድዳችኋል. ይህንን ቪዲዮ ተመልከቱና የራሳችሁን አስተያየት መስጠት ትችላላችሁ. እኔ ግን ልቤን በጣም ነው የነካችኝ. ከራስ በላይ ወንድምን መውደድን እና ፍቅር ሞትን እንደማይፈራ አስተምራናለችና. ሊንኩን በመጫን ቪዲዮውን ይመልከቱ.

http://youtu.be/E2UE4GWfB58